22120015

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Thursday 10 May 2012 (morning)
Jeudi 10 mai 2012 (matin)
Jueves 10 de mayo de 2012 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.
- The maximum mark for this examination paper is *[25 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est *[25 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[25 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2012

*ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።*

**1.**

ዕድሜዬ አራት ዓመት ከአራት ወር ከአራት ቀን ሲሆን እምዬ በሰሙ ወደ ደብተራ እንደብልሃቱ ወስዳ ለትምህርት አስገባችኝ። የቀኑ ልክ ይህን ያህል ተጠንቅቆ የተጠበቀበት ምክንያት በአራት ዓመት ከአራት ወር ከአራት ቀን ትምህርት የሚጀምር ልጅ ትምህርት ይቀናዋል የሚል አስተሳሰብ በዚያ ዘመን ስለነበረ ነው።

መጀመሪያ እንደ ገባሁ የዕድሜ እኩዮቼን በአንድነት ተሰብስበው በማየቴ ደስ አለኝና ለጨዋታው ስል ለጥቂት ሳምንታት ሳልሰለች ተመላለስሁ። እንግዲህ ፊደል ተጀመረ። ፊደሉም በሚጠቀለል ብራና በጉልህ ተጽፎ ከዲልዲላ አባቴ ዘንድ የተላከልኝ ነበር። አባቴ በዚያን ጊዜ ዜማ እያስተማሩ ዲልድላ ማሪያም ነበሩ። ይኸውም እንጦጦ ማሪያም ማለት ነው። በዚያ ጊዜ ዲልዲላ ወይም እንጦጦ እየተባለ በሁለት ስም ይጠራ ነበር።

ደብተራ እንደብልሃቱ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖች እርሱ ራሱ ፊደሉን አስጀመረኝ። በኋላ ግን በወምበር ገፍ ሌላ ፍደል አቆጣሪ አዘዘልኝና ተማር ተባልሁ።አስተማሪው ወደ ፊደሉ ሲያመለክተኝ የኔ ዓይን የሚያየው ወደ በኋላ ልጆቹ ጨዋታ ብቻ ነበር። እስክለማመድ ድረስ ጥቂት ቀን ታገሡኝና ከዚያ «ፊደሉን እያየህ ተማር» እያለ በቁንጢጥ ያደብነኝ ጀመር። ደብተራ እንደብልሃቱም ተማሪዎቹን የሚቀጣበት አንዲት አለንጋ ነበረችውና ያችን እያወዛወዘ «ኋላ አይሆንም አቀምስሃለሁ፣ ፊደሉን እያየህ ተማር» ብሎ አስፈራራኝ። እኔም ያን ልማዴን አልተው ስላልሁ በዚያች አለንጋ ይሸነቁጠኝ ጀመር። ከዚያ በኃላ ትምህርት የተባለውን ነገር በፍጹም ጠላሁና ወደ ተማሪ ቤቱ አልሄድም ብዬ ዘመዶቼን አስቸገርሁ። እነርሱም እየደበደቡና በግድ እየጎተቱ ወሰዱኝ። ይሁን እንጂ ጥላቻው እየባሰብኝ ሄደና ፊደሉን ብቻ ሳይሆን የትምህርት ጓደኞቼን እንኳን ለማየት እስከ መጥላት አደረሰኝ።

እንዲያውም ፊደል ተማር የሚሉኝ ከሆነ በበደበጅ ገደል ዥው ብዩ እገባለሁ እያልሁ ለጓደኞቼ አጫወትኋቸው። በተለይም ሣህሌ እንደብልሃቱ የሚባለው የአስተማሪዬ ልጅ የቅርብ ጓደኛዬ ነውና ገደል ልገባ ነው ብዬ በቁም ነገር አማከርሁትና እንላቀስ ጀመር። ሣህሌ የአስተማሪዬ ልጅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የዕድሜ እኩያዬ ስለሆነ በጣም እንፋቀር ነበር። የበደበጅ ገደል የሚባለውም ከቤታችን በስተምዕራብ የሚገኝ ሁለት መቶ ሜትር ያህል ርዝመት ያለው ትልቅ ገደል ነው።

ከዚህ በኋላ አሳቤ ሁሉ ገደል ለመግባት ወይም ወደ እናቴ ዘንድ ለመኮብለል ብቻ ሆነ። እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ ያለችው መስቀለሶስ በሚባል በደጋው አፋፍ ላይ መሆኑን ዐውቅ ነበር። አንድ ጊዜም ከእምዬ በሰሙ ጋር ወደዚያው ወጥተን ነበርና መንገዱን ለአንድ ጊዜ አይቼዋለሁ። በጉዳዩ ካሰብሁበት በኋላ ገብቶ መሞት አስፈራኝና ወደ እናቴ ቤት መኮብለልን መረጥሁ። መስቀለሶስ የተባለው ስፍራ የጥንት ስሙ መስቀለ ክርስቶስ ነው። እስከ ግራኝ ወረራ ድረስ መስቀለ ክርስቶስ የሚባል ቤተ ክርስቲያን ነበረበት። ግራኝ አጥፍቶታል። አሁን ግን በስፍራው ላይ አንድ አሮጌ የወይራ አጸድ ብቻ ይገኛል።

አንድ ቀን ወደዚያ ተማሪ ቤት ሄጄ ዋልሁና ለምሳ ተመለስሁ። ምሳ ከበላሁ በኋላም ወደ ተማሪ ቤት እንደምሄድ ዓይነት ከቤት ወጣሁና ሽቅብ ወደመስቀለሶስ ጉዞ ጀመርኩ።ከኋላዬ የሚይዘኝ ሰው የተከተለኝ እየመሰለኝ በየጊዜው እገላመጥ ነበር። የመጀመሪያውን ዳገት ወጥቼ ዳኖት ከሚባለው ቀጣና ደረስሁ። ይኸውም የእነመምሬ አብቴና የነአቶ ላቀው መንደር ነው። የመንደሩ ሰው እንዳያየኝ የሚጥሹን ቅጠል ከለላ እያደረግሁ ሁለተኛውን ዳገት ተያያዝኩት። በዚያ በገረረ የፀሐይ ሙቀት ስለተዳከምኩ አለከልክ ነበር። የሆነ ሆኖ ለመመለስ ተስፋ አልነበረኝምና ማረፊያ ከሚባለው ከላይኛው ቀጠና አፋፍ ደረስሁ። ይህ ስፍራ መንገደኞች ብርቱውን ዳገት ጨርሰው የሚያርፉበትታቦ ነው። እኔም እዚያ ስደርስ ከፀሐይ ሙዘት እንዲጋርደኝ የትልቁን ቋጥኝ ጥላ ተገን አድርጌ ተጋደምሁ። አንድ ሰአት ያህል እዚያ ተኝቼ እፎይ ካልኩ በኋላ፣ የቀረኝን መንገድ ቀስ በቀስ ተጉዤ ማታ ለዓይን ሲይዝ መስቀለሶስ ከእናቴ ቤት ገባሁ።

መርስኤ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ትዝታዬ፣አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፣(2008)።

– ፀሀፊው ትምህርት ቤቱን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ቴክኒኮች የትኞቹ ናቸው?

– የህጻናት ቅጣት እንደምን እንደቀረበና ለጽሁፉ ያደረገውን አስተዋጽኦ ግለጽ

– በጽሁፉ የደራሲው ሰብእና እንዴት ቀረበ?

– ጸሃፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት በግልጽ ያቀረበበት መንገድ ላይ አስተያየት ስጥ።

**2.**

ሆነሽኝ የሌሊት ናፍቆት - የኔ ብራ ድምቡል ዶቃ
ነይ ዝቅ በይ እንጎቻዬ - ውቧ ቆንጆ ብርሃን ሳንቃ፣
ጥንት ድሮ የሰጠሽኝ - የምወደው ያ ብርቅ ዕቃ
ወርቅ ዘመን ልጅነቴ ድንገት ወድቆ ተፈረቃ::
ጥብቆዬን አንጠልጥዬ ላንቺ ጊዜ ሽሚያ ሩጫ
ምስጥሬን የሌቱን እውነት - የዓይንሽን ካይኔ ፍጥጫ
ያጓጓኝ ነበር በሲቃ - ወር ጥበቃው ያንቺ መምጫ::
ከዚያ ከዚህ ተጠራርተን - ተሰባስበን ምሽት ማታ
በመንደራችን መስክ ላይ - አዙሪት ድርችም ጨዋታ፣
ሰኞ ማክሰኞ ምክቶሽ - ጠጠር ቅልቦሽ በሆታ
ከባልንጀሮቼ ጋር - እያሞገስንሽ በተርታ
እንዘምርልሽ ነበር - በፍቅር በሳቅ ሁካታ::
እንዲህ እያልን:-
ጨረቃ የኔ ዕቃ' ቃ - ጣይልኝ ስጭኝ ዶቃ
-ሰጠሽኝ ተፈረቃ'
ጨረቃ የኔ አሎሎ
ነይልኝ ቶሎ ቶሎ...

የምሽት ድባብ ጧፌ - የነፍሴ ባትሪ ላምባዲና
የሩቅ መንገዴ ችቦ - የልሜ ሩጫ መሪ ፋና፣
ከድምቀትሽ ወጋገን በቀር - ሙቀት ሰጥተሽ ባትለግሽኝ
የመንገዴን ፈር 'ንጅ - ስንቅ አብስለሽ ባታድይኝ:
ነይ የኔ ደማቅ ባልጩት - እንጫወት ዙር ዕቃ'ቃ
የሌቴ ንግሥት አውራ - እመት ጠፏ ጨረቃ::
አድሎ የሌለሽ ፋኖሴ - ባክሽ ዛሬም ነይልኝ
እንደያኔው በጮራሽ - ጨለማዬን ግፈፊልኝ::
የፅልማሞት ድንጋጭ ጮራ - ድብርት አልባ ትካዜ
አንቺ ነሽ የኔዋ ኮከብ - አሎሎ ቀንዲል መቅረዜ::

ውዳላት ገዳሙ፣ «ላምባዲና»፣ ስደተኛ ግጥሞች ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣**(2003)**::

– ገጣሚዋ ጨረቃን ያቀረበችበት ቴክኒኮች የትኞቹ ናቸው?

– ገጣሚዋ የህ|ናት ግጥም በግጥሙ ውስጥ ማስገባትዋ ጥቅሙ ምንድነው?

– ስለግጥሙ ያለህን አጠቃላይ አስተያየት ስጥ::